# *“አውራ አምባዎችን በግማሽ ሰአት”*

“...የከልክሌ ሚስት የፈተለችው፣
የሸረሪት ድር አስመሰለችው፤
ሸማኔ ጠፍቶ ማሪያም ሰራችው፤
እስኪ ለማሪያም እዘኑላት፣
አመት ተመንፈቅ አለቀላት...”



**ይህ ወትሮ በሆያሆዬ (ቡሄ) ወቅት የምናውቀው የስነ ቃል፣ በአውራ አምባ ማህበረሰብ ውስጥ ቅኝቱ እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፡-**

“የደመቅች ባል፣ አያ ከልክሌ፣ ቀጭን ፈታዩ፣
የሸረሪት ድር አስመሰለው...”

ወንድ ልጅ እንዝርት ይዞ፣ ጥጡን መዞ፣ እና አጡዞ ቀጭን ይፈትላል። ሴቷ ደግሞ እርፍ ጨብጣ፣ ማሳውን በማረሻ ገለባብጣ፣ ታርሳላች። ወንድ ሊጥ አቡክቶ፣ ምጣድ አስምቶ ሲጋግር ማየትም አይገርምም በአውራ አምባ። ሁሉም እንደየችሎታው ነዋ የሚሰራው። “ሴትም ወንድም የቤቱ አባውራ ነው” ይላሉ የማህበረሰቡ መስራች ኑምራ ኑሩ። “...የምንበላባትን ሁላ ቀን እንሰራልን” ይህንንም ያሉት እሳቸው ናቸው።

በአውራ አምባ፣ “ዛሬ ሰንበት ነው፣ ነገ ገብርኤል ነው፣ የዙሁር ሰላት አለብኝ፣ የቻፕል ጸሎት...” ብሎ ... የለም። ቤተስኪያን፣ መስጂድ፣ ጸሎት ቤት የላቸውም። አውራ አምባዎች የተደራጀ ያምልኮ ድርጅት (organized religion) የላቸውም። ይህ በሰለጠነው አለምም እየገዘፈ የመጣ ክስተት ነው። ለመዝገብ (ሪከርድ) ያህል አብዛኛው ሰው “ካቶሊክ ነኝ፣ ኢቫንጅሊካል ነኝ፣ ኦርቶዶክስ ነኝ፣ እስላም ነኝ ...ወዘተ” ቢልም፣ ቅሉ የተደራጀ ሃይማኖት የለውም--አብዛኛው ሰው።

ከሁሉም ትኩረቴን የሳበው፣ እና የገረመኝም በአንድ የአካባቢው ገበሬ *(የአውራ አምባ አባል ያልሆነ)* እና አባል ከሆኑት ጋር የተደረገ አጭር ክርክር ነው፡-

ሰውየው በአውራ አምባዎች የስራ ባህል፣ ሞራላዊ እሴት፣ በጥቅሉ መተዛዘንና መደጋገፍ፣

ስነ-ምግባር ... የተመሰጠና የተማረከ ይመስላል። ችግሩ ሁሉ “... እግዚሃር ይመስገን፣ አልሃምዱሊላሂ፣ እየሱስ ጌታ ነው...” አለማለታቸው እና ከነዚህ ሁሉ አንዱ ወይም ሁሉም የአምልኮ ቦታ (ቤተስኪያን፣ መስጂድ፣ ጸሎት ቤት...) የሌላቸው መሆኑ ይመስላል።

http://www.viewchange.org/videos/awra-amba

ሰውየው ቀጠለ:- “...ወደ ሃይማኖት የሚመጡልን ከሆነ ግን፣ አገሪቱን በሙሉ እናሸበርቃታለን ባይ ነኝ...”

ከሃይማኖት ጋር ስንት ዘመን ኖርን? ... ዛሬ የት ነን?
ለነገሩ የአውራ አምባዋ ወጣት (እናነይ?) መልሷ አጭር ነበር:- “በተግባር መተዛዘን፣ መደጋገፍ ነው--በአውራ አምባ...”

ሰውየው:- “የሃይማኖት ጥያቄ ...ጥላቻ ሳይሆን፣ እናንተ ወይ ቤተስኪያን የላችሁ... የእምነት ቦታ የላችሁ፣ እናንተ የምታምኑት በስራ ነው...”

ሃይማኖት የጥሩ ሰብእና እና/ወይም ሞራል መሰረት ከሆነ፣ መተዛዘንና መደጋገፍም ከሆነ፣ እኔ በአውራ አምባዎች ‘ሃይማኖት’ ለመጠመቅ የመጀመሪያው እሆናለሁ።

የአውራምባዋ እናነይ:- “ እግዚአብሄር የሚገኘው የትም ቦታ ነው። ፈጣሪ ስንተኛም፣ ስንቀመጥም ስንበላም... ከኛ ጋር አይለይም። ...ቤተስኪያን/መስጂድ ገብተን ‘ና፣ እዚህ ኑርና አኑሬህ እመጣለሁ...ክፍቸ ስገባ አገኝሃለሁ...’ ብለን አናምንም”። ባጭሩ ‘የተደራጀ ሃይማኖት የለንም’ ነው።

ይህ የተደራጀ ሃይማኖት (organized religion) በሰለጠነው አለምም እየቀረ ነው።
http://www.religioustolerance.org/chr_prac2.htm

ከሁሉም ከሁሉም፣ እናነይ “እግዜር ያለው በውስጣችን ነው...” ያለችው ነው:-ታላቅ አባባል። እኔም ባለችው እስማማለሁ። እያንዳንዳችን የየራሳችን እግዜር ነን። ባጭሩ አንተ የራስህ እግዜር መሆን ትችላለህ። እኔም፡የራሴ፡እግዜር፡መሆንን መምረጥ እችላለሁ። መጥፎ የሰራሁ እለት ደግሞ ሰይጣን እሆናለሁ። ለኔ ሌላ ሰይጣን የለም። ሰይጣንነትም እግዜርነትም በስራህ ነው። መጥፎ ብትሰራ፣ ሰይጣን አልገፋፋሕም፤ ራስሕ ንህ። ደግም ብትሰራ ራስህ ነህ። ይህን በተመለከተ በሚቀጥለው ጽሁፌ በተረት ተረት አስረዳለሁ።

Gelanew-kirar@hotmail.com